ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መልዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር ስድስት ሚያዚያ 2012 ዓ/ም

COVID-19 ለዓምባ ገነንነት አዲስ ሰበብ ይሆን?

በቤት መቆየት ያለው በጎ እና ሊታሰብበት የሚገቡ ሁኔታዎች

# የሕግ ትርጉም መቼ፣ እንዴት እና በማን?



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

## ‹‹አዲሱ እውነታ›› መጥፎ ውርስና ቅርስ ትቶ እንዳያልፍ መጠንቀቅ ያሻል!

በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው በምርመራ የተረጋገጠ ሰዎች በኢትዮጵያ መኖራቸው መገለጽ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ኢሰመጉ ማንኛውም ሰው ሊደረስበት በሚቻል ከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት የመኖር መብት ያለው መሆኑን በመጥቀስ መንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን በመውሰድ ዜጎቹን ከወረርሽኝ ሥጋት እንዲከላከል በድርጅታዊ ልሳኑ እንዲሁም በተከታታይ ባወጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ማሳሰቢያውን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡


የፌደራልና የክልል መንግሥታትም የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል ‹‹ያስችላሉ›› ያሏቸውን የተለያዩ እርምጃዎች መውሰድ ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እንደመሆናችን የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች (በተለይም በመንግሥት በኩል) ሁኔታው ከሚጠይቀው በላይ ሆነው በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የማይገሠሡ ሰብዓዊ መብቶችን እንዳይጥሱ ማሳሰብም ግዴታችን ነው፡፡

ለዚህም ነው ‹‹አዲሱ እውነታ›› መጥፎ ውርስና ቅርስ ትቶ እንዳያልፍ በዚህኛው ዕትም ልናሳስብ የፈለግነው፡፡ ዐውዱ የተለየ ቢሆንም ከ2009 ዓ.ም ወዲህ በአገራችን በተከታታይ

የወጡ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጆች በመንግሥት ኃይሎች ለተፈጸሙ አስከፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምቹ መደላድል መሆናቸው አይዘነጋም፡፡ በመንግሥት የጸጥታ አካላት ዘንድ ስለ ዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ያለው ግንዛቤ ገና ያልዳበረ በመሆኑና ተጠያቂነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለመኖሩ የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ በመከሰቱ ምክንያት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ፖሊቲካዊ ዓላማ ያላቸውን እርምጃዎች ያለ ገደብ ለመፈጸም የሚጠቀሙበት መሣሪያ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያሻል፡፡

ይህን የምንለው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ የበሽታውን ሥርጭት በመከላከል ሰበብ የመንግሥት አካላት በወሰዷቸው እርምጃዎች የሰዎች ሕይወት መጥፋቱን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል በሚወሰደው የጥንቃቄ እርምጃ ላይ በመመሥረት ሐሳቧን የገለጸች አንዲት ሴት መታሠሯን በመታዘባችን ነው፡፡

የ COVID-19ን ሥርጭት ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት መደገፍ አለብን፤ እየደገፍንም ነው፡፡ ነገር ግን «አዲሱ እውነታ» መጥፎ ውርስና ቅርስ ጥሎብን እንዳያልፍ ስናሳስብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጋላጭ የሚሆኑ መጠለያ አልባና የጎዳና ተዳዳሪ ዜጎችን፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን፣ የሌሎች አገራት ስደተኞችንና እሥረኞችን ጨምሮ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ ከሆኑና ድምፃቸውን ለማሰማት ከማይችሉ ሰዎች ጎን ከመቆም ወደ ኋላ ሳናፈግፍግ ነው፡፡




## መልእክተ ኢሰመጉ

### አሳታሚ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org


ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# ሰዋዊ

# COVID-19 ለዓምባ ገነንነት አዲስ ሰበብ ይሆን?

በሱራፍኤል ግርማ

የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል የሚደረገው ዓለም አቀፍ ጥረት ብርቱ የሞት ሽረት ትግል ሆኗል፡፡

አገራት ያላቸውን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት አቀናጅተው በመጠቀም በሽታው እያስከተለ የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ ጉዳት ለመቀነስ ፋታ ባጡበት በዚህ ወቅት የመንግሥት ሚና፤ ጠንካራ አመራር ከመቼውም ጊዜ በላይ ተፈላጊ መሆኑ ተስተውሏል፡፡

ነገር ግን መንግሥታት ይህን የአስቸኳይ ጊዜ ተጠቅመው የሥልጣን አድማሳቸውን ያለ ከልካይ በማስፋት ዓምባ ገነንነት የሰፈነበት ዐውድ እንዳይፈጥሩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋቾች ሥጋታቸውን መግለጽ ጀምረዋል፡፡

እ.ኤ.አ ሚያዝያ 7 ቀን 2020 ለንባብ በበቃው የ«ዘ ጋርዲያን» ዕትም ላይ COVID-19ን መዋጋት እንዳለብን ነገር ግን እየዳኸ ቀስ በቀስ የሚገለጥ የዓምባ ገነንነት አዝማሚያ ከበጎ ጎኑ ይልቅ የሚያደርሰው ጥፋት እንደሚልቅ የሚያሳስብ አንድ ጽሑፍ ወጥቶ ነበር፡፡

የጽሑፉ አቅራቢ የአውስትራሊያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር ኤድዋርድ ሳንቶው አሁን ያለንበትን ሁናቴ ሐዲድ ላይ ወደ ተኙ ሰዎች ያለ ተቆጣጣሪ በአስፈሪ ፍጥነት በሚገሠገሥ ባቡር በመመሰል ነበር ሥጋታቸውን የገለጹት፡፡

COVID-19 ዓለምን በሚያተራምስበት በዚህ ሰዓት ይህ ምናባዊ እንቆቅልሽ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የምንፈተንበት እውነታ ሆኗል፡፡ አንዳች እርምጃ ሳይወሰድ ቢቀር ከሐዲዱ ላይ ያሉ በጣም ብዙ ሰዎች ያልቃሉ፤ ባቡሩ ሐዲድ ስቶ ቢገለበጥ ደግሞ የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር

አነሥተኛ ቢሆንም ታላቅ ቀውስ ይከተላል፡፡ ባቡሩ ኮሮና ቫይረስ ነው፡፡

ከሐዲዱ ላይ ያሉት ሰዎች ደግሞ ችግሩ ከዐቅማችን በላይ ሆኖብን ዐቅመ ቢስ ምስኪን ያደረገን፣ እየተቁለጨለጭን መሪዎቻችንን የምንመለከትና የእነርሱን ውሳኔ የምንጠብቅ ዜጎች ነን፡፡

መሪዎቻችን ባቡሩን ወደ አንድ አቅጣጫ ቢያስቀይሱት ጉልቀኑ መሣፍር የሌላቸው ሰዎች ያለ ጊዜአቸው ይሞታሉ፡፡ ወደ ሌላ አቅጣጫ ቢያስቀይሱት ደግሞ ብዙዎች ከሞት ይተርፋሉ ነገር ግን የዓለም ኢኮኖሚ ከባድ ቀውስ ውስጥ ይገባል፤ ለዓምባ ገነንነትም በር ይከፈታል፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም የሆነው ሀዩመን ራይትስ ዎች ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ኬኔት ሮዝ እ.ኤ.አ ሚያዝያ 3 ቀን 2020 ባቀረቡት ጽሑፍ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ዓምባ ገነን መንግሥታት COVID-19ን እንዴት እየተጠቀሙበት እንደሆነ ተንትነዋል፡፡

ወትሮም ቢሆን ዓምባ ገነናዊ አዝማሚያ ለነበራቸው መሪዎች የኮሮና ቫይረስ የፈጠረው ቀውስ ተቺዎችን ጸጥ ለማሰኘትና ሥልጣናቸውን ለማደላደል አመቺ እንደሆነላቸው ማስረጃ እያቀረቡ ያስረዳሉ፡፡

በኬኔት ሮዝ ገለጻ መሠረት አንዳንድ መሪዎች በቀውስ ወቅት የመብት እቀባ የሚያስከትሉ የመንግሥት እርምጃዎችን በጸጋ ለመቀበል ሕዝብ ፈቃደኛ እንደሚሆን በመገንዘብ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል የሚካሄደውን መጠነ ሰፊ ዘመቻ ተቺዎቻቸውን ለማሸማቀቅ ብቻ ሳይሆን ተቆጣጣሪ የሌለበት ያልተገደበ ሥልጣን ለራሳቸው ለመስጠት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

ዓለም አቀፉ «የጸረ ሽብር» ዘመቻ ለረዥም ጊዜ ጸንተው የቆዩ ዕቀባዎችን በሲቪል ነጻነቶች ላይ ለመጣል ሰበብ ሆኖ እንዳገለገለው ሁሉ ይህን ወረርሽኝ ለመግታት የሚደረገውም ዘመቻ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያጨናግፍ አሉታዊ ውጤት እንዳያስከትል ሥጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬስ ረቡዕ ሚያዝያ 22 ቀን 2020 (እ.ኤ.አ) በሰጡት መግለጫ ዓምባ ገነን መንግሥታት ዓለም አቀፉ ወረርሽኝ የፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም የሰብዓዊ መብቶች

ጥሰቶች እየፈጸሙ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ «በአንዳንድ አገራት ካለው የአክራሪ ብሔርተኛነት፣ ሕዝበኛነት፣ ዓምባ ገነንነት እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዳራ አንጻር ይህ ቀውስ ከወረርሽኙ ጋር ተያያዥ ያልሆኑ ጨቋኝ እርምጃዎችን ለመውሰድ ትክክለኛ ያልሆነ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡» በማለት ሥጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ታውጇ፤ ለዐዋጁ ማስፈጸሚያም ደንብ ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

በጤና መሠረተ ልማት ረገድ እጅግ ኋላ ቀር በሆነችው አገራችን ወረርሽኙ ሊያስከትል ከሚችለው ከባድ ጉዳት አንፃር የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ መታወጁ ተገቢ ቢሆንም ከዚህ በፊት ከወጡ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ አፈጻጸም መጥፎ ተሞክሮዎቻችን አንጻር ሥጋታችንንና ማሳሰቢያችንን ከወዲሁ መግለጽ ተገቢ ነው፡፡ የፌደራልና የክልል የጸጥታ አካላት ይህን የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ሲያስፈጽሙ በማናቸውም ሁኔታና ምክንያት ቢሆን የማይገደቡ የሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት፡፡

# ሰዋዊ

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93 ላይ የሠፈረውን «የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልል መስተዳድሮች የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ፡፡»

የሚል ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ የሚሆን የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ በፌደራል መንግሥት ደረጃ ከመታወጁ በፊት ክልሎች የየራሳቸውን እርምጃዎች ሲወስዱ ቆይተዋል፡፡

ነገር ግን ይህን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን ባልተቀናጀ መልኩ ገቢራዊ ባደረጉ የክልል መስተዳድሮች ድንገተኛ ውሳኔዎች ምክንያት የሕዝብ ማጓጓዣ አገልግሎት ተቋርጦ ብዙ ዜጎች መጉላላት ደርሶባቸዋል፡፡ ይህን መሰሉ የክልሎች የተናጠል እርምጃ ሕዝብን ከማደናገርና ከማጉላላት አልፎ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መንገድ ይከፍታል፡፡

የሕግ አስከባሪዎቻችን ስለ ሰብዓዊ መብቶች ያላቸው ግንዛቤ እጅግ አነሥተኛ በመሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ በሚወጣ ጊዜ ሁሉ ዜጎች ስለ ደኅንነታቸው መሥጋታቸው የተለመደ ነው፡፡

በጸጥታ አስከባሪዎቻችን ዘንድ አድፍጦ የቆየው (በለውጡ ሰሞን ለዝቦ የነበረው) ሥልጣንን ያለ አግባብ ባልተመጣጠነ ሁኔታ የመጠቀም አዝማሚያ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል ከሚካሄደው ዘመቻ ጋርም በተያያዘ በግልጽ መስተዋል ጀምሯል፡፡ ተከታዮቹን ክስተቶች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡-

በትግራይ ክልል «በአስቸኳይ ዐዋጁ የተከለከለ ተግባር ፈጽሟል» የተባለ ሰው በፖሊስ ተገድሏል፣ በማረቆ አካባቢ የአንድ ዓመት ሕፃን ልጅ በጥይት ተገድሏል፣ በጎንደር ከተማ አንድ የባጃጅ ሹፌር በተመሳሳይ ምክንያት እጁ ላይ በጥይት ተመትቷል፣ የኮሮና ቫይረስ ከተገኘበት ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለ ሥልጣናት ለይቶ ማቆያ መግባት እንዳለባቸው ሐሳቧን የገለጸች ወጣት በሀረር ከተማ ታሥራ ቆይታለች፡፡

አሁን ያለንበት ጊዜ ከወትሮው እጅግ የተለየ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በተወሰኑ መብቶችና ነጻነቶች ላይ አስፈላጊና ተመጣጣኝ የሆነ ገደብ መጣሉን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ይፈቅዳሉ፡፡

ነገር ግን ይህን ቀውስ ተጠቅመው የራሳቸውን ፖሊቲካዊ ግብ ለማሳካት የሚሞክሩ ባለ ሥልጣናትን ነቅቶ መጠበቅ ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ከጤናችን ባሻገር እውን ሆኖ ለማየት ብዙ መሥዋዕት የምንከፍልለትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አደጋ ላይ ይጥላሉና፡፡

የተፈጠረው የጤና ቀውስ ማለፉ አይቀርም ይህን አስታክኮ ሥር የሚሰድደው (በአገራችን ዐውድ ደግሞ ይበልጡን የሚባባሰው) ዓምባ ገነንነትና የመብት ጥሰት ግን ወረርሽኙ ትቶ ከሚያልፈው ዘላቂ ውርሶች አንዱ እንዳይሆን ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅብናል፡፡

> <<በአንዳንድ አገራት ካለው የአክራሪ ብሔርተኝነት፣ ሕዝበኝነት፣ ዓምባ ገነንነት እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዳራ አንጻር ይህ ቀውስ ከወረርሽኙ ጋር ተያያዥ ያልሆኑ ጨቋኝ እርምጃዎችን ለመውሰድ ትክክለኛ ያልሆነ ምክንያት ሊሆን ይችላል።>>

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ኬላ

## ሕግ

# የሕግ ትርጉም መቼ፣ እንዴት እና በማን?

ጥበቡ ኃ.

ምርጫ ቦርድ በመጪው ነሀሴ 23 እንዲካሄድ ቀን ተቆርጦለት የነበረውን ምርጫ በተመለከተ ባለፈው መጋቢት 22 ቀን 2012 ዓ.ም ይፋ ያደረገው ውሳኔ ምርጫውን በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት በታቀደለት ጊዜ መከናወን እንደማይችል ያሳወቀ ነበር።

ይኼን ተከትሎ በኢትዮጵያ የሕግ እና የፖለቲካ ባለሙያዎች መካከል የምርጫ መራዘም በሚፈጥራቸው ክፍተቶች ላይ የጦፈ ክርክር ሲደረግ ሰንብቷል፡፡

መንግስት የምርጫው መራዘም ለሚፈጥረው ክፍተት መፍትሔ ይሆናሉ ያላቸውን አራት አማራጮች ይፋ አድርጎ ሲያበቃ፤ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በኩል የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 54/1፣ አንቀጽ 58/3 እና አንቀጽ 93 ከሕገ-መንግስት ዓላማ እና ግቦች እንዲሁም መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ለማስተሳሰር ትርጉም ይሰጥባቸው ሲል ወስኗል፡፡

ለመሆኑ የሕግ ትርጉም ሲባል ምን ማለት ነው? ሕግን መተርጎም ለምን ያስፈልጋል? እንዴትስ አድርገን ነው መተርጎም የሚገባን? እና ሕገ-መንግስትስ እንደምን ይተረጎማል? የሚሉትን በጽንሰ-ሀሳብ ደረጃ እንደሚከተለው በአጭሩ እናያለን፡፡

## መልካም ጊዜ!

በመሠረቱ ሕግ የተሰራበትን ዓላማ ለማሳካት ሲባል ግልጽና ምክንያታዊ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ይህ ግን ሁሌም የሚሳካ ባለመሆኑ የሕግ ትርጉምን አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች አልፎ አልፎ ይፈጠራሉ፡፡

የሕግ ትርጉም ማለት በአጭሩ የሕጉን ግልጽ ያልሆነ ክፍል እውነተኛ ምንነት መፈለግ ማለት ነው፡፡ ሙሉጌታ በላይ የተባሉ የሕግ ባለሙያ “ሕግ ማለት በትረጉም ጀርባ ላይ የታዘለ ህጻን ነው” ይላሉ፡፡ ሕግ በባህሪው ተለዋዋጭ (dynamic) በመሆኑ በየጊዜው በትርጉም እየታሸ የሚፋፋ ወይም የሚያድግ ነው ልንል እንችላለን፡፡

ለመሆኑ ሕግን መተርጎም ለምን አስፈለገ ያልን እንደሆነ ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን፡፡

የመጀመሪያው ከቋንቋ ተፈጥሯዊ ባህሪ የሚመነጭ ነው፡ ፡ ይኸውም ሕግ አውጪው በሕግጋቱ ውስጥ ያሰፈረውን እውነተኛ ዓላማ ማወቅ የሚቻለው በቃላት በመሆኑ ሲሆን፤ ቃላት ደግሞ በባህሪያቸው አሻሚ እና አጠራጣሪ በመሆናቸው ነው፡፡

ከዚህም ተሻግሮ ቃላት የሕግ አውጪውን እውነተኛ ፍላጎት አስፍተው ሊገልጹ ወይም በበቂ ሁኔታ ሳይገልጹ ሊቀሩ የሚችለበት መንትያ አደጋ መኖሩ ሁለተኛው ምክንያት ነው፡፡

ሌላኛው ደግሞ የሰው ልጅ የእውቀት ስፋት ውስን እና የተገደበ በመሆኑ፤ ሕግ አውጪው የሰውን ልጅ እያንዳንዷን ጥቃቅን ግንኙነቶች መቆጣጠር የሚችል ሕግ ማዘጋጀት ስለማይችል ሆን ብሎ በወቅቱ ያልታሰቡ አዳዲስ ሁኔታዎችን ወደፊት ለማስተናገድ በሚል ለትርጉም ክፍት የሆኑ ጥቅል አገላለጾችን የሚጠቀም መሆኑ ነው፡፡

የሕግ ትረጉምን፡- ለትርጉም በምንጠቀምበት ስልት መሠረት ሰዋሰዋዊ ትርጉም (grammatical interpretation) እና አመክንዮአዊ ትርጉም (logical interpretation) ወይም ትርጉሙን የሚሰጡትን ተቋማት መሠረት በማድረግ ትምህርታዊ ትርጓሜ፣ በፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትርጓሜ እና በሕግ አውጪው የሚሰጥ ትርጉም ብለን በዓይነት ከፋፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡

በመጀመሪያው ዓይነት መደብ ሰዋሰዋዊ ትርጓሜ ማለት ለሕጉ የምንሰጠው ትርጉም በራሱ በሕጉ ውስጥ ባሉት ቃላት የተለመደ እና ተፈጥሯዊ ትርጉማቸው ላይ መሠረት አድርጎ መደረግ እንዳለበት የሚያበክር ነው፡፡

በአንጻሩ አመክንዮአዊ ትርጓሜ ደግሞ የሕግ ትርጉም ከሕጉ ቃላት ውጪ ተሻግሮ በመውጣት የሕግ አውጪውን እውነተኛ ዓላማ ወይም ሌላ ዓይነት አጥጋቢ ማስረጃ በመፈለግ ትርጉም እንዲሰጥ የሚያሳስብ ነው፡፡

በሁለተኛው መደብ ደግሞ ትምህርታዊ ትርጓሜ (Doctrinal interpretation) የምንለው በሕግ

ምሑራን እና ባለሙያዎች አማካኝነት በምርምር መጻህፍት፣ በክፍል ውስጥ በሚደረጉአካዳሚያዊክርክሮችእናበመሳሰሉትየሚሰጥየሕግትርጓሜንነው፡፡

የፍርድ ትርጉም (Judicial Interpretation) ማለት ደግሞ አንድ ፍ/ቤት በፊቱ የቀረበለትን ጉዳይ ለመወሰን ሊጠቀመው ያለው ሕግ ጥያቄ ውስጥ የገባ እንደሆን የሕጉን ምን ማለትነት በማየት

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

ለተያዘው ጉዳይ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መወሰን ማለት ነው፡፡

እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው ነገር የሕጉ ትርጉም አከራካሪ ያልሆነ እንደሆነ፤ ፍ/ቤቱ ሕጉን መተግበር እንጂ መተርጎም አያስፈልገውም፡፡

ሌላኛው ሕግ ተርጓሚ አካል ደግሞ እራሱ ሕግ አውጪው (Legislative interpretation) ነው፡፡ በጥንታዊ ስርዓት ዳኞች የሕጉ ምንነት ባጠራጠራቸው ወይም ባከራከራቸው ጊዜ ንጉሱ ትርጉም እንዲሰጥበት ያደርጉ ነበር፡፡

በዚህኛውም ዘመን ይኸው ልማድ ቀጥሎ የሕግ አውጪ ም/ቤቶች ግልጽ አይደሉም ወይም አሻሚ ናቸው የተባሉ ሕጎችን ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

## የሕገ-መንግስት ትርጉም

ሕገ-መንግስት በብዙ ልዩ ነገሮቹ ምክንያት እንደሌሎች ሕጎች ዓይነት ባለመሆኑ የትርጉም ሒደቱም የተለየ ነው፡፡

ሕገ-መንግስት በራሱ የብዙ ሰዎች ውጤት እንደመሆኑ በሕገ-መንግስት ትርጓሜ ውስጥ ትልቁ አስቸጋሪ ነገር ትርጉም የሚሰጠው የጸሃፊዎቹ (ሕጉን ያዘጋጁት ሰዎች) ወይስ የአጽዳቂዎቹ (የዜጎች፤ ተወያይተው ያጸደቁት) እውነተኛ ፍላጎት ነው የሚለው ነው፡፡

ሌላው የሕገ-መንግስት ትርጓሜ አስቸጋሪ ነገር ማን ይተርጉመው የሚለው ነው፡፡ ሀገራት በሚከተሉት ፍልስፍና፣ ባለፉበት ታሪካዊ መንገድ እና በፖለቲካዊ ኃልዮታቸው ላይ መሠረት አድርገው የተለያየ ዓይነት ሕገ- መንግስት ተርጓሚ አላቸው፡፡

በዚህም መነሻነት በአንዳንድ ሀገራት መደበኛ ፍ/ቤቶች ሕገ-መንግስት የመተርጎም ሥልጣኑ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ በሌሎች ደግሞ ተለይተው የተዘጋጁ ሕገ-መንግስታዊ ፍ/ቤቶች ይህን ሥልጣን ለብቻቸው ይይዙታል፡፡

በሦስተኝነት ደግሞ ፖለቲካዊ የሆኑ ተቋማት ይህንኑ ሥልጣን ይዘውት እናገኛለን፡፡ በኢትዮጵያ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 62 (1) እና 83 (1) ሕገ-መንግስቱን የመተርጎም ሥልጣኑን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ይሰጣል፡፡

ምክር ቤቱ ሥራውን እንዲያግዘው በጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት እና ም/ፕሬዝዳንት የሚመራ ስድስት የሕግ ባለሙያዎች እና ሦስት የፌደሬሽን ም/ቤት አባላት ያሉት የሕገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ የተሰኘ ተቋም እንደሚመሰረትም የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 82 ያስቀምጣል፡፡

ይህ ብዙዎች እንደሚያምኑት ም/ቤቱ የሚሰጠው የሕገ-መንግስት ትርጉም በሕግ ባለሙያዎች እና በፖለቲከኞች መካከል ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡

## ሕግ እንዴት ይተረጎማል?

በብዙ ሀገራት የሕግ ስርዓት ውስጥ ሕግ እንዴት መተርጎም እንደሚገባው በጊዜ ሒደት የዳበሩ ደንቦች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉትን እንደሚከተለው በአጭር በአጭሩ እናያለን፡፡

## ወርቃማ የትርጓሜ ደንብ / the golden Rule of Interpretation

ይህ የትርጉም ደንብ ቃላት በራሱ በሕጉ ውስጥ ባላቸው አገባብ እና ጥቅም ሊተረጎሙ እንደሚገባ ያሳስባል፡፡

የፍ/ቤቶች ዋናው ተግባር የሕግ አውጪውን ዓላማ ማረጋገጥ በመሆኑ፤ ግልጽ እና አሻሚ ያልሆኑ ቃላትን ሰዋሰዋዊ ትርጉም በመስጠት ብቻ መተርጎም አለባቸው፡፡ ከላይም ለመጥቀስ እንደሞከርነው ይህ ደንብ በአጭሩ ሰዋሰዋዊ ትርጓሜ ማለት ነው፡፡

## የኢጁስድም ጀነሪስ ደንብ / the Ejusdem Generis Rule

በዚህ ደንብ መሠረት "ሌሎች አንቀጾች እንዳሉ ሆነው" በሚሉ ክፍት አገላለጾች በሙሉ ያንን አንቀጽ የሚዛመዱትን ወይም የሚተሳሰሩትን አንቀጾች ለማለት እንደሆነ ተደርጎ ሊተረጎም ይገባል የሚል ነው፡፡

በአጭር ምሳሌ ለማስረዳት አንድ ሰው ሚስቱን ወደ ገበያ ስትወጣ ቅቤ፣ ወተት፣ እንቁላል እና ሌላ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ግዢ ብሎ ቢነግራት፤ በዚህ የትርጉም ደንብ መሠረት የእንስሳት ተዋጽዖዎችን እንጂ እንደ ሽንኩርት ወይም የቤት እቃ ያሉትን ነገሮች ግዢ ለማለት ፈልጎ እንዳልሆነ ተደርጎ መተርጎም ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

## የሚስቺፍ ደንብ / the Mischief Rule

ይህ ደግሞ የሕግ አውጪው እውነተኛ ዓላማ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ የተገኘ የሕግ ቋንቋ ወይም አገላለጽ ፍርድ ቤቱ ሕጉ የተዘጋጀበትን ታሪካዊ ሒደት፡ ከማርቀቅ እስከ ማስጸደቅ የነበረውን ሒደት ከግምት በማስገባት ትርጉም እንዲሰጥበት የሚል ደንብ ነው፡፡ አዋጁ የተዋወቀበትን እና በመጨረሻም ሕግ ሆነ ፡፡

## አመክንዮአዊ የትርጉም ደንብ / Logical Interpretation

ይህን ደንብ የምንጠቀመው የሕጉን ትርጉም በሰዋሰዋዊው ትርጓሜ ማሳካት ያልቻልን እንደሆነ ነው፡፡

በሕጉ ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት አሻሚ ከሆኑ እና የሕግ አውጪው እውነተኛ ፍላጎት የትኛው ስለመሆኑ ጥርጣሬ ከገባን ሕጉ አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለመከላከል አመክንዮአዊ ትርጓሜ እንዲሰጥ ማድረግ እንችላለን።

እንግዲህ በጽንሰ-ሀሳብ ደረጃ የሕግ ትርጓሜ ምንነት በአጭሩ ይህን ይመስላል፡፡ ሰሞኑን በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ በብዛት ሕገ-መንግስት፣ ሕገ-መንግስታዊ፣ የሕግ ትርጉም የመሳሰሉት ቃላት በብዛት ስንሰማቸው

የምንውል በመሆኑ ሀሳቦቹን በጥቂቱም ቢሆን ለመረዳት እንዲያስችለን ያዘጋጀሁትን ጽሁፍ በዚሁ አበቃሁ፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም

## የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ምክንያት በቤት መቆየት ያለው በጎ እና ሊታሰብበት የሚገቡ ሁኔታዎች

ዳን ይርጋ

### 1. መግቢያ

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) በዓለም ላይ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የበርካታ ሰዎችን ህይወት ነጥቋል አሁንም ከኤዢያ እስከ አውሮፓ ከአሜሪካ እስከ አፍሪካ ቁጥሩ ከሀገር አገር ይለያይ እንጂ የበርካቶችን እየቀጠፈ የሚገኝ አደገኛ ገዳይ ቫይረስ ነው፡፡

ይህ ፅሁፍ በሚዘጋጅበት ወቅት በዓለም ላይ በኮሮና ቫይረስ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር 4,048,967 (Corona Virus cases) ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር 277,434(Deaths) እንዲሁም ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር ደግሞ 1,405,049 (Recovered) ነው 1 ፡፡

### 2. ቫይረሱ ያስከተለው ቁሳዊና ሰብዓዊ ጉዳቶች

የዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት ስለ ኮሮና ቫይረስ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝነቱን ያወጀው እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 5 2020 ዓ.ም ነው ይሁንና ቫይረሱ ለመጀመሪያ ጊዜ በቻይና ውሀን ሁቤ ከተማ መከሰቱ የታወቀው እ.ኤ.አ ዴሴምበር 31 2020 ዓ.ም. ነው ከዚህም ጊዜ ጀምሮ ከ277,000 (ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ሺ በላይ) ሰዎች ሞተዋል 2 ፡፡

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በአለም ላይ ያደረሰውን የኢኮኖሚ ጉዳት በሚመለከት የተባበሩት መንግስታት የንግድና ልማት ኤጀንሲ ሪፖርት መሰረት እስከ አሁን በዓለም ላይ ወደ አንድ ትሪልየን ዶላር የሚገመት የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ጉዳት በኮሮና ቫይረስ ምክንያት እንደደረሰ ሪፖርት አውጥቷል 3 ፡፡

### 3. የኮሮና ስርጭት አሁን ያለበት ሁኔታ

የቫይረሱ ስርጭት ቁጥር የዓለም አቀፍ ሁኔታ በሚመለከት ከላይ በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን ይህ ቁጥር ምንም እንኳን በአንዳንድ ሀገራት አዳዲስ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም በዓለም አቀፍ ደረጃ አሁንም በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎችና በዚሁ በሽታ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው ያለው በዚህም ምክንያት አሁንም የዓለም አቀፍ የጤና ስጋትና ፈተና መሆኑ እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ቁጥር በሚመለከት ይህ ፅሁፍ እየተዘጋጀ እስካለበት ጊዜ ድረስ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 210፣ የሞቱ ሰዎች ቁጥር 5 ሲሆን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ደግሞ 97 ነው 4 ፡፡

### 4. ስርጭቱን ለመቆጣጠር እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች

የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመቆጣጠር መንግስት የተለያዩ ጥረቶች ሲያደር ቆይቷል አሁንም በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡

ከተወሰዱት እርምጃዎችና ጥረቶች ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ከማወጅ አንስቶ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሰዎችን በመመርመር እንዲሁም በለይቶ ማቆያ ውስጥ ማስገባት፣ የተለያዩ ህንፃዎችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ ትላልቅ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን ወደ ለይቶ ማቆያና እንዲሁም ለታመሙ ሰዎች ማከሚያነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተዘጋጅተዋል 5 ፡፡

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ተፅዕኖ መገላጫው በኢኮኖሚ፣ በጤናና በማህበራዊ ላይ ብቻ አይወሰንም የፈጠረው ጫና ከዚህም ከፍ ብሎ የፖሊቲካ ሁኔታዎችም ላይ ጫና ፈጥሯል የዚህም ማሳያ በዓለም ላይ በርካታ ሀገራት በዚህ ወቅት ሊያካሄዱ አቅደውት የነበሩትን ምርጫ በኪሮና ቫይረስ ጫና ምክንያት ወደ ሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ተገደዋል ኢትዮጵያም በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በዚህ አመት ልታካሄድ አቅዳ በርካታ ዝግጅቶች ሲካኄዱ ቆይቶ በመጨረሻም የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት በሚል ይህን አገር አቀፍ ምርጫ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫው መካሄድ እንደማይችል አሳውቋ፡፡

ስለቫይረሱና የመተላለፊያው መንገዶች እንዲሁም ሊወሰድ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በተለያየ መንገድ የማስተማሩ ሂደት በስፋት እየተሰጡ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በርካታ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሰራተኞች የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ስርጭትን ለመግታት ስራቸውን ከቤታቸው ሆነው ነው በመስራት ላይ የሚገኙት፡፡

### 5. በቤት ውስጥ መቆየት

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ስርጭትን መግታት ከሚቻልባቸው መንገዶች

ውስጥ አንዱ የምህበራዊ ርቀትንና አካላዊ ቅርርብን ማስቀረት ነው ይህንንም ጥንቃቄን ደግሞ በተሸለ መልኩ ማከናወን የሚቻለው በቤት ውስጥ በመቆየት እንደሆነ የጤና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ አበክረው ይመክራሉ፡፡

የኮሮና ስርጭትን ለመግታት በቤት ውስጥ መቆየት በርካታ በጎ ጎኖችና ጥቅሞች እንዳሉት ሁሉ የማይናቅ ተግዳሮቶች አሉት፡-

## 5.1. በጎ ጎኖቹ

በቤት ውስጥ መቆየት ቫይረሱት ለመግታት በባለሙያዎች የሚመከርና በተለይም በንኪኪ ለቫይረሱ (COVID-19) የሚኖር መጋለጥን የሚቀንስ ነው የጥንቃቄ እርምጃ ነው በተጨማሪም በርካታ ጠቃሚ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል

ከዚህም ውስጥ

- ለቤተሰብና ለግል ህይወት በቂ ጊዜ የማግኘት እድልን ይፈጥራል፣
- በግል የሚሰሩ የተለያዩ ስራዎች ለመስራት ያስችላል፣
- በቤት ውስጥ የሚሰሩ የተለያዩ ስራዎችን፣ ፈጠራዎችንና ሞያዎችን ለመልመድና ለማከናወን ይጠቅማል፣
- የተለያዩ ፅሁፎችን ለማንበብ እንዲሁም ለመጻፍ ጭምር ይጠቅማል ...ወዘተ

## 5.2. አዳጋች የሚያደርጉት ሁኔታዎች(ሊታሰብበት የሚገቡ ሁኔታዎች)

በቤት ውስጥ መቆየት በሀገራችን ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሁኔታ ለበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም በቀን ገቢ ለሚተዳደሩ ዜጎች እጅግ በጣም ከባድ ነው ምክንያቱም ከቤት ወጥተው ስራ ሰርተው ካልገቡ የዕለት ጉርሳቸውን ማግኘት አይችሉም ስለሆነም በስራቸው የሚተዳደሩ የቤተሰባቸውንም የእለት ጉርስ ጭምር ማሳጣት እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም፡፡

ስለሆነም የኮሮና ቫይረስን (COVID-19) ስርጭት ለመግታት ሁሉም ሰው በቤቱ ይቆይ ብሎ ማሰብ የነዚህን አይነት የህብረተሰብ ክፍል በህይወት የመኖር መብት አደጋ ውስጥ እንደመጣል ነው የሚቆጠረው፡፡

በተጨማሪም መኖሪያ ቤት ፈፅሞ የሌላቸው ዜጎች ቁጥር በጣም በርካታ ነው እነዚህም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩት በጎዳና ላይ ተበትነው በልመና ነው የሚተዳደሩት ስለሆነም ቤት ያለው በቤቱ ሲቆይ ቤት የሌለው ደግሞ የት ሊገባ ነው የሚለው ብርቱ ጥያቄ ሚዛናዊና ሰብዓዊ የሆነ መልስ ይፈልጋል ስለሆነም በቤት መቆየት በአንድ መልኩ በጎ ጎኖችን እንደሚፈጥር ሁሉ ለሌሎች በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ህይወት አደጋ ውስጥ የሚጥል መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

መንግስት የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል አቅም በፈቀደ መጠን የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል ይህ የሚበረታታ ማንም ድጋፍ ሊሰጥበት የሚገባ ስራ ነው ይሁንና እነዚህን ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት ሌላ የመብት ጥሰት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በአንዳንድ የለይቶ ማቆያ ወስጥ የገቡ ሰዎች የሚያነሷቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ረገድ አሁንም ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት ይኖርበታል በተጨማሪም አሁን ባለው ሁኔታ የተለመደ ስራቸውን መስራት ያልቻሉ ዜጎች በተለይም በአነስተኛ የስራ ዘርፍ የተሰማሩና አቅመ ደካማ የሆኑ ዜጎችን በማገዝና በመደገፍ ረገድ የተጀመሩ ስራዎች በስፋትና በተጠና መልኩ መሰራት የሚችልበት መንገድ ይታሰብበት እላለሁን፡፡

ቸር ያሰማን!'

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

---

1 1 https://www.worldometers.info/coronavirus
2 2 www.who.int/news-room/detail/27-04-2020-who-timeline----covid-19
3 3 www.weforum.org/agenda/2020/03/corona/trade-economics date 17 March 2020
4 4 www.moh.gov.et Date may 09/2020
5 5 በመንግስት የተቋቋመ ግብረ ሀይል ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለሀብቶች ጋር በትብብር እየተሰራ ያለ ስራ ነው